የዚህ ትዕይንት አካል ሁነን፣ ዝማሬያቸውን እየዘመርን ትርጉም እንድምታ ያለው ሕይወት ወደሚወረስበት የገድል የደም ጎዳና ማምራት የዚያ የጀግና ትውልድ የአጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ክፋይ የሆንን ሁሉ ዕድል ፈንታችን ዕጣ ተርታችን ነው ይላል ኢሕአፓ::-

ለፋሽስቶች የሚሠፈረበትን የየካቲት ቁና ቀድመውን ያለፉት ታጋዮች በዙ ዘር አዙረውናል:-ቀሪው ዘር እኛን ቀሪዎቻችን ይጠባበቃል:- የቁናው ዘር እንዲሞላና ቁናቸውን እንዲያገኙ እምነታችን ሰበዝ አከርማ፣ አንድነታችን አለላ ሁኖ መቅረብ ይጠበቅበታል::-

አሁንም አሁንም አንዱ የካቲት አልፎ ሌላ የካቲት ሲተካ- ኢሕአፓ በትግሉ ላይ ያለው አቋም የማይተካና የማይለወጥ ነው::-

የካቲት በሕዝባዊ ዐመፅ ይወለዳል!

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን !!!